# እነ አቦይ ስብሃት ያላደረጉትን

# የትግራይን ህዝብ ዶ/ር አብይ ያድኑት ይሆን?

መቼም የኢትዮጵያ ህዝብ ደግ ነው፤ ደግነቱ አያልቅበትም። ይህን ሁሉ ግፍ ይፈፀምበት የነበረውን ኢህአዴግ አነደዚህ በከፍተኛ ችግር ውስጥ በገባበት ወቅት ችግሩን በሰላም እንዲፈታ ምኞቱን ይገልፅለት ነበር። ለዚህ ነው ብዙ ኢትዮጵያውያን ዶ/ር አብይ አህመድ የወያኔ የኢህአዴግ መሪና የሃገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር እንዲሆኑ መመረጣቸውን በበጎ አይን የሚያዩት። አዎን ዶ/ር አብይ የኢህአዴጉ OPDO ልጅ ናቸው። ከዚህ ድርጅት ጋር ለረጅም ጊዜ ቆይተዋል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከህዝብ ጎን ቆመው ድምፃቸውን ሲያሰሙ የታዩበት አጋጣሚ አልነበረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የኢህአዴግ በተለይም የወያኔ ሃርነት ትግራይ መሪዎች ሲያጣጥሉት የቆዩትን የኢትዮጵያዊነት መንፈስ በድርጅቱ ውስጥ እንዲያገግም የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርጉ፤ ድርጅታቸውን OPDOንም ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ መልክ ሲያደራጁ አይተናል። ይህ በኢህአዴግ ታሪክ ያልታየ ክስተት ከOPDO አመራሮች መታየት ሲጀምር ኢትዮጵያዊነትን የሚያመልከው ክፍል ሁሉም ብሄረሰቦች በአኩልነት ተከባብረው እንዲኖሩ የሚመኘው ህዝብ በኢህአዴግ ዙሪያ ያሉትን እንቅስቃሴዎች በልዩ ትኩረት እንዲመለከተው አደረገው። እንዲያውም በአለፉት ጥቂት ወራት የተቃዋሚ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ከመከታተል ይልቅ በኢህአዴግ ዙሪያ ያለውን ንትርክና እንቅስቃሴ በልዩ ትኩረት ሲከታተል ቆይቷል።

ይህ በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረ ችግር ከኢህአዴግም አልፎ በሃገሪቱም ላይ አደጋ የሚያስከትል በመሆኑ የተለያዩ ትንተናዎች የሚቀርቡበት ቢሆንም በአብዛኛው የወያኔ ኢህአዴግ መዳከምና በወያኔዎች ጎራ ተሰሚነት ያለው መሪ አለመኖሩ ነው የሚል አመለካከት አለ። አዎ ይሄ የለም ባይባልም ከምንም በላይ ጎልቶ የወጣው ችግር ግን ወያኔያዊ የጠባብ ብሄርተኝነት ስሜት እየሞተ መምጣቱን ነው።ወያኔ ሃርነት ትግራይ በውስጡና በፈጠራቸው ድርጅቶች ውስጥ ይህን የጠባብ ብሄርተኝነት ስሜት በመፍጠር ድርጅቶቹን በአሽከርነት ሲጠቀምባቸው ቆይቷል። የብዙዎቹ የኢህአዴግ ወለድ ድርጅቶች መሪዎች የሚመለመሉት በወያኔ ሃርነት ትግራይ ድርጅት መሪዎች ነበር። በፈለጉ ጊዜ ይሾሙዋቸዋል በፈለጉ ጊዜም ይሽሩዋቸዋል። የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ምንም አይነት ነፃነት ያልነበራቸው አሻንጉሊቶች ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ሁሉም አባል ድርጅቶች ያለምንም አንፃራዊ ነፃነት የወያኔ ሃርነት ትግራይ መሪዎች በሚፈልጉት መንገድ እየነጎዱ እነሱ የሰጡዋቸውን አስተሳሰብ ከማንፀባረቅ አልፈው በክልላቸው የሰፈረውን የሌላውን ብሄረሰብ አባል ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን ብሄረሰብ አባላት ሲያሰቃዩ ቆይተዋል። ከቀያቸው የተፈናቀሉትና የተገደሉትም ቁጥር በቀላሉ የሚታይ አይደለም። እንዲያውም አንዳንዶች ድርጅቶች ከሌላ ብሄረሰብ መሪ በትውስት እየተሾመላቸው መሳቂያ ሆነው ቆይተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይም ወጣቶችና የተማሩት በኢህአዴግ ድርጅቶች ውስጥ በመግባታቸው ይህ የወያኔ ማን አለብኝነት ተቀባይነት እያጣ መጣ። በተለይ ኦሮሞውን ይወክላል በሚባለውና አማራውን ይወክላል በሚባሉት ድርጅቶች ውስጥ ከውጭ ያለውን የህዝብ ድምፅና እንቅስቃሴ ማስተዋል የሚጀምሩ መሪዎች ብቅ ብቅ ማለት በመጀመራቸው ወያኔ ከዚህ በፊት ይጠቀምበት የነበረውን ትምክት የሞላው ማናለብኝነት እና በጥቅም አስሮ መገልገል ሙሉ በሙሉም ባይሆን በከፊል ዋጋ እያጣ መጣ። ይሄም ሂደት እያደር ከወያኔዊ አመለካከት ጋር በመጋጨቱ የድርጅቶቹ መሪዎች የችግራቸውን መንሳኤ እንዲመረምሩ አስገደዳቸው። በተለይ በጎንደር ከዚያም በባህርዳርና በሌሎች ከተሞች በተደረጉት ሰላማዊ ሰልፎች ወጣቶቹ የወልቃይት ጠገዴን ህዝብ ጥያቄ ከማንፀባረቅ ባሻገር ለኦሮሞው ፤ ለቤንሻንጉሉ፤ በአጠቃላይ ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ሙብት መከበር በድፍረትና በጀግንነት ሲሚገቱ በመታየታቸው እንቅስቃሴውን ይበልጥ እንዲጠናከር አደረገው።

ይሄ በኦሮሞውና በአማራው ወጣቶች ጀግንነት የሚድረገው እንቅስቃሴ በወያኔ ኢህአዴግ አባል ድርጅቶች ውስጥ በመሪነት የተቀመጡትን ሃይሎች የሚኮረኩር ስሜት ከመፍጠር አልፎ አንገታቸውን ቀና አድርገው እንዲያዩ እድል ሰጣቸው። ከዚህም በላይ ከዚህ በፊት ለረጅም ጊዜ የተቀበሉትን የወያኔን አስተሳሰብ በመጋፋት ከብሄራቸው ወጣ ብለው የኢትዮጵያዊነትን ዋጋ ከፍ አድርገው እንዲያዩ አስገደዳቸው። ይህም በጠባብ ብሄርተኝነት ላይ የተመሰረተው ወያኔያዊ አስተሳሰብ ወድቆ ኢትዮጵያዊነት እንዲነሳ በር ከፈተ። በተለይ የሶማሌ ክልል ታጣቂ ሃይሎች በኦሮምኛ ተናጋሪዎች ላይ ያደረጉት ከፍተኛ ጥቃት ለኦሮምኛ ተናጋሪ የፖለቲካ ሊቃውንት ከፍተኛ መልዕክት ነበረው። በታሪክ ኦሮሞዎች በተናጠል የተጠየቁበት ጊዜ አልነበረም። የአማርኛ ተናጋሪዎች እና የኦሮምኛ ተናጋሪዎች ሲጠቁም ሆነ ሲያጠቁ ተለያይተው አያውቁም ነበር። ሆኖም ግን በወያኔው አስተሳሰብ በተናጠል እንዲቆሙ ተደርጎ ተራ በተራ መጠቃታቸው የወያኔያዊ አስተሳሰብ ውጤት መሆኑን የOPDO መሪዎች የተረዱት አሁን ይመስለኛል። ወያኔም ቢሆን ይህን ጥቃት ማስቆም አላቃተውም። ግን ኦሮሞዎችን ለማስፈራራት የተጠቀመበት ዘዴ ነበር። "ይሄን እንቅስቃሴያችሁን ትታችሁ ከኔ ጎን ካልተሰለፋችሁ በዚህ መልክ ትጠቃላችሁ" በማለት ለማስፈራራት ነበር። ነገር ግን በተቃራኒው ኦሮሞዎች ይህ የወያኔ ጥቃት መሆኑን ከመረዳታቸውም በላይ ከአማርኛ ተናጋሪው ህዝብ ጋር ያለው ታሪካዊ ትሥሥር የህልውናውን ጥያቄ የሚመልስ መሆኑን አወቁት። የአንድነት ሃይሎች እንደተናገሩት አማራም ሆነ ኦሮሞ ተነጣጥሎ ሊኖር እንደማይችል በአስተማማኝ ያረጋገጠ አጋጣሚ ነበር።

እንግዲህ ይህን በመሰለ ታሪካዊ ወቅት ከወያኔ ኢህአዴግ የኦሮሞ ክንፍ OPDO የወጡት ዶ/ር አብይ የድርጅቱ ሊቀመንበርና የሃገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር እንስኪሆኑ ድረስ የነበረውን ውጣ ውረድ ራሳቸው የኢህአዴግ መሪዎች በተለያየ መልክ ይገልፁታል። የኢህአዴግ ፅ/ቤት ሃላፊ አቶ ሺፈራው ሽጉጤ በሚሰጡት መግለጫ እጅግ አሳፋሪ የሆነ ገለፃዎችን በተደጋጋሚ ሰምተናል። በአንድ በኩል "በድርጅቱ ውስጥም ሆነ ድርጅቱ ለሃገሪቱ በሚሰጠው አመራር ዲሞክራሲያዊ መንገድ የመከተል ችግር ስለነበረበት ተሃድሶ እያደረግን ነው" ካሉ በኋላ ምርጫውንና ስብሰባውን ሲገልፁ ደግሞ "በኢህአዴግ መንገድ፤ በኢህአዴግ ባህል፤ በታላቁ መሪያችን ራእይ ላይ ተመስርቶ የተካሄደ ስለነበር ኢህአዴግ አሸናፊ ሆኖ ወጥቷል። " በማለት ከላይ የተናገሩትን ገለፃ በመፃረር ይደሰኩራሉ። ይህን በጣም አሳዛኝና አሳፋሪውን ንግግራቸው ዶ/ር ደብረፅዮን በነጋታው ሲያጋልጡት ስብሰባው የተካሄደው በተለመደው የኢህአዴግ አሰራር መልክ እንዳልነበረና የምርጫው ስርአትም የተለየ እንደነበር በቲቪ ቀርበው ገልፀውታል። እኒህ አቶ ሺፈራው አብዮታዊ ዲሞክራሲ እያሉ በተደጋጋሚ ሊያላግጡ ቢሞክሩም ይህን "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ትርጉም የሚያውቁት አይመስለኝም፤ ይህን "ፍልስፍና" የሚደግፍ ምንም አይነት ታሪካዊና ሳይንሳዊ እውቀትም ሲቀርብም ሰምተን አናውቅም።

አዎ፤ የአሁኑ የስልጣን አያያዝ እስከ አሁን ከነበሩት የተለየ መሆኑን እንስማማለን። አቶ መለስ ወደ ስልጣን የወጡት ተቃዋሚዎችንም ሆነ በኢህአዴግ ዙሪያ የተሰለፉትን ጀሌዎች በያዙት ነፍጥ አስገድደው ነው። ያኔ ወያኔ ሀርነት ሰራዊት በፍፁም የበላይነት ከላይ እስከታች  የተቆጣጠረበት ወቅት ነበር። ለሆዱ የተሰለፈው ብቻ ሳይሆን እድሜውን ትንሽ ለማቆየት የሚፈልገውም ፖለቲከኛ ይሄን በድፍረት ለመቃወም አልዳዳውም። እርሳቸውም ስልጣን ከያዙ በኋላ በማናአለብኝነት የኢህአደግን መንጋ እየነዱ በፈለጉት መልክ የመምራት እድል ነበራቸው፤ መንጋውም እየተሰደበም እየተዋረደም ታማኝነቱን አልነፈጋቸውም።

አቶ ሃይለማርያም ወደ ስልጣን ሲወጡ ደግሞ እሳቸው እችለዋለሁ ይገባኛል ብለው ሳይሆን የወያኔ ሀርነት ትግራይ መሪዎች "አይዞህ እኛ አለንልህ" ብለው ነበር ጎትተው ያስቀመጡዋቸው። ይህም በመሆኑ አምስት አመት ሙሉ እራሳቸውን ሳይሆኑ ክርስቶስን ረስተው በየቀኑ "ባለራእዩ መሪያችን" እያሉ ፀሎት እያደረጉ መሸከሙ ሲያቅታቸው ቦታውን ለቀዋል። በስልጣናቸው ዘመን አንድም አይነት ችግር ለመፍታት ሳይሞክሩ "የበታች አለቆቻቸው" በሚሰጡዋቸው ትዛዝ አስቾኳይ አዋጅ እያሳወጁ የራሳቸውን ህገ መንግስት እየጣሱ የሀገራችን ችግር እንዲወሳሳቡና ለባሰ ችግር እንድንዳረግ አደረጉን። አንድ ቀን መሪ መሪ ሳይሸቱ የኢትዮጵያን ህዝብ ማሰፈራቸውን ታሪክ መዝግቦት ይኖራል።

ወደ ዶ/ር አብይ የስልጣን ሂደት ስንመጣ መነገር ያለበት ብዙ ታሪካ ቢኖርም ለዚህ ፅሁፍ የሚመጥነውን ያህል ባነሳ ደስ ይለኛል። ዶ/ር አብይ እንደ አቶ መለስ ጠመንጃ ደግነው እያስፈራሩ ተመረጡ ብሎ የሚናገር ሰው እንደማይኖር እርግጠኛ ነኝ። እንደ አቶ ሃይለማርያም ከአንገታቸው ላይ በገመድ ታስረው ተጎትተው መጡ የሚልም የለም። እንደተለመደው ከፍተኛ ወታደራዊ ትጥቅ ያለውን ሃይል የሚያዙት የወያኔ ኢህአደግ መሪዎች "አይዞህ እኛ አለንልህ" ብለው ሞራል ሰጥተው አቀረቡዋቸው የሚልም ያለ አይምስለኝም። እንዲይውም እኒህ ሰው እንዳይመርጡ ከፍተኛ ዘመቻና ዱለታ ተደርጎባቸው እንደነበር ብዙ መረጃዎች አሉ። የወያኔ መሪዎች በተለመደው መልክ ያገለግሉናል ብለው አቶ ሺፈራው ሽጉጤን አዘጋጅተው መቅረባቸው ደግሞ በይፋ የሚታወቅ ነው። ወያኔዎቹ ድምፃቸውንም ለአቶ ሺፈራው ስጥተው ነበር ግን አልተሳካላቸውም። ለነገሩ የወያኔ ሀርነት ትግራይ መሪዎች ያልተማሩበትና ያልተገነዘቡት ነገር አለ። በአሁኑ ወቅት የነሱ ቡድን በአስተሳሰብም ሆነ በቁመናው ጥራት የሌለው እንኳንስ ሌላውን ሊያሳምን በውስጣቸው እንኳ ባንድ መቆም ያቃታቸው መሆኑን ገና አልገባቸውም። ይሄን ያልተረዱት የወያኔ ሀርነት ትግራይ መሪዎች ስብሰባን በስብሰባ እያበራከቱ ስብሰባዎችን በማራዘም ከዚህም አልፎ ግለሰቦችን በነገር በመውጋት የተለያዩ ችግሮችን ለመፍጠር ቢሞክሩም ሳይሳካላቸው ቀርቶአል፤ ወያኔን ወክሎ ለመሪነት የተወዳደሩት ግለሰብም 1% ድምፅ አግኝተው ከከፍተኛ ውርደት ጋር ሽንፈትን ተከናንበዋል። በአንፃሩ ዶ/ር አብይ ወደዚህ ስልጣን የመጣበት መንገድ በጣም ግልፅ በመሆኑ ብዙ ማውራት አይኖርብኝም። ግለሰቡም ሆነ ድርጅቱ (OPDO) በጥበብና የአስተሳሰብ ለውጥ በማድረግ ከድርጅታቸው አልፈው በሌሎች ድርጅቶችም ታማኒነትን ለማግኘት የተጓዙት መንገድ ቀላል አልነበረም። ለዚህ ውጤት የOPDO አመራሮች የሚመሰገኑ ቢሆንም ከሁሉም በላይ ሊመሰገኑ የሚገባቸው የብአዴን("አማራው")  አመራሮች ናቸው። ምንም እንኳ ቁጥራቸው ባይበዛም ከደቡብ ድርጅቶች አመራር ውስጥ አቶ ሺፈራውን በመቃወም ለዶ/ር አብይ ድምፅ የሰጡ አመራሮች መኖራቸውም ይነገራል። ይህ ደግሞ ልዩ ምስጋና የሚያሰጥ ነው። ብአዴን ግን የተሰጠውን  ትእዛዝና የነበረበትን ግፊት ተቋቁሞ በታሪኩ የመጀመሪያውን ቁምነገር እንደሰራ የሚመዘግቡለት ከመሆኑም በላይ በአማራና በኦሮሞ ህዝብ ማህል የተጀመረውን መቀራረብ ለማጠናከር ከዚያም አልፎ ለራሱ ለብአዴን ህልውና የሚበጅ ስራ መስራቱን እንዲያውቀው ይገባል። ይሄም ክስተት የተፈጠረው ከውስጥ ከኢህአደግ ወለድ ድርጅቶች ውስጥ የወጣቶችና የተማሩ ሰዎች ቁጥር እያየለ በመምጣቱና በውጭ ደግሞ ወጣቱ ትውልድ በጀግንነት የሚያደርገው ትግል የሚከፍለው መስዋእትነት የፈጠረው ተጽዕኖ ነው።

ዶ/ር አብይ የኢህአደግ ሊ/መንበርና የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆናቸው ጥቅሙ ለማን ነው፤ በዚህ ዙሪያ ላይ ያለኝን አስተሳሰብ ትንሽ ላንሳ

1ኛ የመጀመሪያው ጥቅም ለኢህአደግ ነው። ኢህአደግ በታሪኩ የህዝብን ቀልብ የሳበ መሪ ለመጀመሪያ ጊዜ አግኝቷል። በኢህአደግ ታሪክ የመጀመሪያው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ተካሂዷል። ኢህአደግ ቅንና በራሱ የሚተማመን መሪዎች የሌለው

በመሆኑ ወደመፈራረሱ እየሄደ ያለ ድርጅት ነው። ወያኔ ሀርነት ትግራይ ነፍጥዋን ተማምና በተለመደው ተንኮል ካላደናቀፈች ኢህአደግን በአዲስ መልክ ጠፍጥፎ በመስራት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ለማስታረቅ እድሉን ያገኙት መሪ ዶ/ር አብይ ናቸው ። ስለዚህ ኢህአደግ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመታረቅ ድርጅታዊ ህልውናውን ማስቀጠል ከፈለገ በአዲሱ መሪ የሰላምና እርቅ አጀንዳ አቅርቦ የሁሉንም ህዝብ ሙብት ለማክበር መነሳት አለበት። ሰለዚህም ኢህአዴግ የኢሥፓ ዕጣ እንዳይደርሰው ይህን እድል ሊጠቀምበት ይገባል፤ ከዶ/ር አብይም ከፍተኛ አስተዋይነት እና ጥበብ ይጠበቅባቸዋል።

2ኛ በሁለተኛ ደረጃ የዶ/ር አብይ ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆን በዋነኛነት የሚጠቅመው ለትግራየ ህዝብ ነው። የትግራይ ህዝብ የሚበላውንና የሚጠጣውን ብቻ ሳይሆን ልጆቹን እየሰጠ ለስልጣን ያበቃቸው የወያኔ ሀርነት ትግራይ መሪዎች ከድትውታል። ከሚወዳት ኢትዮጵያና ከሚወደውና ከሚያከብረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አኮራርፈውታል። ዛሬ የአሉላ አባነጋ ልጆች ኢትዮጵያዊነታቸው አጠያያቂ እንዲሆን አድርገውታል። በዚህ መልክ ከቀጠለ በመላው ኢትዮጵያ የተሰራጩት ትግርኛ ተናጋሪዎች ህይወት አደጋ ላይ ነው። በወያኔ ሀርነት ትግራይ የተበደለውና የተገፋው ህዝብ ቁጣ በምን መልክ እንደሚገለፅ አይታወቅም። ምንም እንኳ ትግራይ ትልቋ እስር ቤት ብትሆንም የትግራይ ተወላጆች በሚካሄደው ትግል ውስጥ ያላቸው ሚና ዝቅተኛ በመሆኑ ትልቅ ቅሬታ አለ። ስለዚህ በዚህ ወቅት አንድ ችግር ቢፈጠር ትግረኛ ተናጋሪው ህዝብ ሊቋቋመው የማይችል ችግር ይገጥመዋል። መቼም አሁን ዶ/ር አብይ ይህን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት ይህ አደጋ ከመከሰቱ በፊት ሃገራዊ እርቅ እንዲፈጠር በድርጅቱ ውስጥ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ አድርገው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት የሚታይባት አገር እንድትሆን፤ ሁሉንም የኢትዮጵያ ሃይሎች የሚያሳትፍ ፖለቲካዊ መፍትሄ ይፈጥራሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ይሄም የትግራይን ህዝብ ከከፍተኛ ጥፋት ያድናል።

3ኛ በሶስተኛ ደረጃ የማስቀምጠው በተለይ የኦሮሞን ወጣቶች ነው። እነዚህ ወጣቶች ለብዙ አመታት ትክክለኛ በሆነም ትክክለኛ ባልሆነም የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እየገቡ ከፍተኛ መስዋእትነት ሲከፍሉ ቆይተዋል። በታሪካችን የኦሮሞ ልጆች በኢህአደግ ዘመን ያለቁትን ያህል አልቀው አያውቅም። ከዚህ ሁሉ እልቂት በኋላ የትግል መስመራቸው ጥራት እያገኘ ከመሄዱም በላይ ከመንግስት ጋር የተሰለፉ የድርጅት መሪዎች ሳይቀር ትግላቸውን መደገፋቸው ትልቅ ድል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ከኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ከፍተኛውን ድርሻ ከያዘው ከኦሮሞ ህብረተሰብ የተወለዱት ዶ/ር አብይ የሃገሪቱ ጠ/ሚኒስቴር መሆን ሌላ የትግሉ ውጤት ነው ብዬ አምናለሁ። ይህም በመሆኑ ዶ/ር አብይ እንደ ጎርፍ በየመንገዱ ሲፈስ የቆየውን የኦሮሞ ልጆች ደም ዳግም እንዳይታይ ለማድረግ ጠንክረው ይሰራሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህም ማለት በብሄረሰቦች ማህል መከባበርና መተማመንን ለመገንባት እድሉ ከጃቸው በመሆኑ እንዲጠቀሙበት ታሪክና ትውልድ አደራ ይላቸዋል።

4ኛ- በጥቅሉ የመከራ ጽዋ ሞልቶ ሲፈስባት የቆየችውን ኢትዮጵያ ማንሳት እፈልጋለሁ፤ ትውልድ ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ ህይዎቱን ለግሶ ያስተላለፈልንን አገር ባለፉት 27 አመታት እንደጠላት እንድንቆጥር እየተቀሰቀስን ቅስቀሳውን ያልተቀበልን ተገደን እንድንሸከመው እየተደረገ፤ ኢትዮጵያዊነት ክብር መሆኑ ቀርቶ እንደ ውርደት ተቆጥሮ በዓለም መዛበቻ ሆነን፤ ችግራችን በመፍታት በእኩልነትና በሰላም እንዳንኖር አንዱ የሌላው ጠላት እእንደሆነ እየተነገረን በፍርሃትና በጥርጣሬ የጎሪጥ እየተያየን እንድንኖር በወያኔ ኢህአዴግ ተወስኖብን፤ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በከተማም በገጠርም ደማችን ሲያፈሱት ህይወታችን ሲቀስፉት የነበሩት የወያኔ ኢህአዴግ መሪዎች ዛሬ ጉዳቸው ፈልትዋል፤ ዛሬ በወያኔ ኢህአዴግ ውስጥ የቆየውን እንቶ ፈንቶ በታኝ ሰበካ አንቀበልም ኢትዮጵያዊነት ክብራችን ነው ለዚህም አያቶቻችን ህይወት ገብረዋል የሚሉ ሃይሎች እያበቡ መጥተዋል፤ ከውጭ ደግሞ ወጣቱ ትውልድ ሞትን ሳይፈራ ለሃገሩ ለሙብቱ ለወገኑና ለማንነቱ በጀግንነት መታገሉን ቀጥሎአል። ዛሬ ከውስጥም ከውጭም ለወያኔ በቀላሉ የሚንበረከክ ሃይል የለም፤ በእስር የቆዩት የህሊና እስረኞች እነ እስክንድር ነጋ እነ አንዱዓለም እነ በቀለ እነ ንግስት የህዝቡን ሞራል ማነሳሳት ብቻ ሳይሆን ትልቅ የጀግንነት ትምህርትም ሰጥትዋል።

ይህ ዕድል ለዶ/ር አብይ ትልቅ ጉልበት ሊሆናቸው ይችላል፤ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ በድፍረት ኢትዮጵያ እንደ ሃገር መቀጠል አለባት ብሎ የሚናገር መሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ከኢህአዴግ ወለድ መሪዎች አንደበት ሲወጣ በመስማታችን እኛም ጉድ ብለናል። ባለፉት አመታት ገና አቶ መለስ በህይወት በነበሩበት ወቅት ጊዜ ጀምሮ ሃገራችን ኢትዮጵያ በችግር አዘቅት ውስጥ እየዳከረች መሆንዋን እራሳቸው ኢህአዴጌችም ሲነግሩን ሲነግሩን ቆይተዋል፤ ታዲያ በየዓመቱ ችግሩን የፈጠረው የኢህአዴግ አመራር ስለሆነ ኢህአዴግ እራሱ መፍትሄ ያመጣል እያሉ በየመድረኩ ቢቀባጥሩም የኢትዮጵያ ችግር እራሱ ኢህአዴግ በመሆኑ መፍትሄ ፈላጊ ነኝ ማለቱ ትልቅ ቧልት ነበር። ወያኔ ኢህአዴግ ብቃት ያላቸውን የሃገሪቱን ልጆች ሲያስፈልገው በማሰር ሲፈልግ ከፖለቲካው መድረክ ብቻ ሳይሆን ከሃገርም በማግለል ጠመንጃውን ተጠቅሞ ከስልጣን ላይ መቆየቱን ማንም የሚያውቀው ነው። አወን ለኢህአዴግ በስልጣን መቆየት ሌላው አስተዋጽዖ ያደረገው ሃይል የተቃዋሚው ክፍል ልፍስፍስነት ነው፤ ይታያችሁ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች በሌለ የስልጣን ወንበር ሲጋጩ እና ድርጅቶቻቸውን

እየከፋፈሉ አባላትን ሲያተረማምሱ እያዘን አይተናል። ጥርት ያለ የፖለቲ መስመር ያላቸው ድርጅቶች እንዳሉ ብናውቅም አንዳንዶቹ ደግሞ የፖለቲካውን ሀ፡ሁ ያውቃሉ ለማለት ያስቸግራል አንዳንዶቹ ወያኔን ኮሚንስቶች ናቸው ይላሉ ወሸኔ ኮሚኒስት በምንም ታምር ጠባብ ብሄርተኛ ኮሚኒስት ሊሆን አይችልም፤ ሌሎቹ ደግሞ የትግራይ ብሄርተኛ ናቸው ይሉዋቸዋል እኔ ግን በዚህም አልስማማም፤ ወያኔ የትግራይን የብሄርተኝነት አጀንዳ ለተወሰነ ጊዜ ይጠቀምበት እንጂ የለየለት የማፍያ ቡድን ነው።

በእርግጥ ከትግራይ ጋር የሚያተሳስረው ገመድ ቢኖርም በዋናነት የቡድንና የግል ጥቅማቸውን የሚያግበሰብሱ ግለሰቦች እና ቡድኖች ስብስብ ነው፤ ለትግራይ ህዝብ የሚያስብ ቡድን ቢሆንማ ኖሮ ወያኔ በሰራው ስህተት የትግራይ ህዝብ እንደዚህ አይነት አደጋ በሚያንዣብብበት ወቅት ኢትዮጵያን ይቅርታ ጠይቆ የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖረውን ምቾት ያስተካክል ነበር፤ ወያኔ ግን አጥፍቶ መጥፋት የሚሉትን የአምባገነኖች መርህ ያነገበ ቡድን በመሆኑ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ለማሰብ ጊዜ የለውም።
አወን ባለፉት 27 ዓመታት የትግረኛ ተናጋሪው ኅብረተሰብ በተለይ የወያኔ ደጋፊዎች በልዩ ልዩ መልክ የተለያዩ እድሎችና ቅድሚያ እየተሰጣቸው ሲጠቀሙ ለመቆየታቸው አንካካድም፤ ይሄን ደግሞ የሚያደርጉት የወያኔ(ትግሬ) ባለሰልጣኖች ብቻ ሳይሆኑ አድርባዮቹ ኦሮሞዎች፤ አማራዎች፤ እንዲሁም ደቡቦች የኢህአዴግ ባለስልታኖችም ጭምር ነበር፤ አረ እንዲያውም ከዚህም አልፈው የወያኔ ሃርነት ትግራይን መሪዎችን ለማስደሰት ወገኖቻቸውን ሲደበድቡ ሲያስሩ ሲያሳዱ እና ሲገሉ ቆይተዋል።

በታሪካችን የትግረኛ ተናጋሪው ህዝብ እንደ አሁኑ ወቅት በጥርጣሬ አይን ታይቶ አያውቅም፤ ከዚህም አልፎ አሁን አሁን ወያኔ ሃርነት ትግራይ እየበደለን ነው የሚሉት ሃይሎች የበቀል ኢላማ ሊያደርጉዋቸው የሚችሉበት እድል በጣም ሰፊ እየሆነ መጥትዋል። ይህን አደጋ የወያኔ ኢህአዴግ መሪዎች የሚያውቁ ቢሆኑም በጥቅም ስለሰከሩ በህዝቡ ላይ እያንዣበበ የመጣውን አደጋ ለማየት አልፈለጉም። ወያኔ ሃርነት ትግራይ ለትግራይ ህዝብ የምትከፍለው ውለታ ይሄ መሆኑን ስናይ የድርጅቱን ዝቅጠት ፍንትው አድርጎ ያሳየናል፤ ለነገሩ የሚገርም አይደለም የወያኔ ሃርነት መሪዎች አገር ወዳድ የትግራይ ልጆችን ኢዲዩ ናቸው ኢሕአፓ ናቸው እያሉ አሳደው በመግደል ትግራይን ካጸዱ ቦኋላ ደርግ ከለገሰላቸው የስልጣን ኮረቻ ላይ ወጥተው ለትግራይ ህዝብ መብት እና ጥቅም እናስከብራለን እያሉ ያቅራሩ እንጅ ባለፉት 27 አመታት በድርጅታቸው ስር ከፍተኛ ንብረት በማካበት የመሪዎቹ ቤተሰቦች እና ወዳጆች ሚልየነር ሲሆኑበት ታዬ እንጅ አሁንም የትግራይ ህዝብ በየመንገዱ ሲለምን ይታያል፤ ያውም ከውርደት ጋር።

አዎን እዚህ ላይ አንድ ነገር እንዲያዝልኝ እፈልጋለሁ የወያኔ አባል እና ደጋፊ ነን የሚሉት ትግረኛ ተናጋሪዎች በሚደረግላቸው ልዩ እንክብካቤ በሚሰጣቸው ሰፊ ዕድል ከብረዋል ተምረዋል በስልጣንም እየተንደላቀቁ ቆይተዋል፤ አዎን ትግራይ ውስጥ የወያኔ ተቋሞች እና ድርጅቶች ከፍተኛ ገንዘብ በማፈሰስ አንዳንድ ለውጦችን አድርገዋል፤ መንገዶች ተሰርተዋል፤ ወዘተ ወዘተ ግን ይህ ሁሉ ከወያኔ ሃርነት ጥቅም አንጻር የተደረገ ለውጥ ነው፤ በዚህ ወቅት ብዙውን ኢትዮጵያዊ በጣም የሚያሳዝነው ጉዳይ ቢኖር የትግራይ ሙሁራን በአብዛኛው ድምጻቸውን አጥፍተው በህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል በሃገር ላይ እያንዣበበ የመጣውን አደጋ በጎሪጥ ሲያዩ መቆየታቸው በጣም ያተዛዝባል፤ አወ እንደነ አብርሃ በላይ እንደነ አረጋዊ በርሄ የመሳሰሉ ቁጥራቸው ጥቂት የሆኑት ወገኖች ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ ይታወቃል ግን ብዙዎቹ ወይ ውስጥ ውስጡን ይደግፋሉ ወይም "አልሰማሁም" ብለው ፊታቸውን አዙረው ተቀምጠዋል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ የሚቃወሙ መሰለው ቢታዩም ተቃውሞዋቸው የወያኔ ሃርነት ትግራይ መሪዎችን ቦታ ለመተካት እንጂ በሃገር አጥፊው የወያኔ ሃርነት ትግራይ የፖለቲካ አጀንዳ ላይ አይደለም።

በጣም ይገርማል እውነቱን ከተነጋገርን አሁን አሁንኮ ቁጥሩ ቀላል ያልሆነ የሃገራችን ህዝብ በተለይ ወጣቱ "በቃ ተከባብረን መኖሩን ካልፈለጉ ይሂዱ ይሂዱ ይገንጠሉ ከነሱ ጋር መኖር አልጠቀመንም_" የሚለው ሰው ቁጥር ቀላል አይደለም፤ አንዳንዱ ደግሞ ገና ትግረኛ የሚናገር ሰው ሲያይ ደሙ ይፈላል። ይሄ ወያኔ ሃርነት ትግራይ የዘረጋው የፖለቲካ መስመር የፈጠረው ችግር ነው ፤ ይህ ሁሉ መከራ በትግረኛ ተናጋሪዎቹ የፖለቲካ መሪዎች እና የጦር ጀኔራሎች የመጣ መሆኑን ስለሚያምን እንደዚህ አይነት ስሜት ቢፈጠርበት አይገርምም። ከዚህ ለመላቀቅ በሚወሰደው እርምጃ ምስኪኖቹ የትግራይ ተወላጆች ለአደጋ ተጋላጭ መሆናቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት ወያኔ ሃርነት ትግራይ እራስዋን ማስተካከል ሲገባት ሁለት ወር ሙሉ ተሰብስበው እንደ እቃቃ ጭዋታ ቀላል የሹምሽር አድርገው ከመጡ ቦኍዋላ ችግሩን ሁሉ ያዳፈኑ መስሎዋቸው አዲስ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጃቸው እጅግ አሳፋሪ ነው። ይህ አዋጅ አደጋ አርግዞ መጣ እንጂ በምንም ታምር የለውጡን ማእበል አያቆመውም።

እንግዲህ በዚህ ወቅት ነው ዶ/ር አብይ የወያኔ ኢህአዴግ ሊቀመንበር የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስተር ሆነው ብቅ የሚሉት፤ ለእርሳቸው መጥፎ ጊዜ ነው እንደዚህ የተፍረከረከ ድርጅት መምራት ከባድ ነው፤ ወያኔ ሃርነት ትግራይ እንደ አቶ ኃይለማርያም ከአንገታቸው ላይ ገመድ አስራ ወደ ፈለኩት አቅጣጫ እመራሃለሁ በማለት ባትፈታተናቸውም ባጋጣሚ የያዘችውን የመረጃ እና የመከላከያ ኃይል በመጠቀም በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ ደንቀራ እንደምትሆንባቸው ይጠበቃል፤ በወያኔ ፍቃድ የተቋቋመው የሚንስትሮች ምክር ቤት በሙሰና የዳሸቀው ቢሮክራሲ ከፍተኛ የራስ ምታት ነው፤ ከሁሉም በላይ አዋጁ እና አዋጁን ለማስፈጸም የተቋቋመውን ኮማንድ ፖስት  ምን እንደሚያደርጉት አላውቅም። አወ እነዚህን ተሸክሞ ደግሞ ለውጥ ማምጣት አይቻልም።   እነዚህን ሁሉ ለመቋቋም ደግሞ በቂ አቅም አይኖራቸውም፤  ይህ አቅም የሚገኘው ተቃዋሚዎችን እና የኢትዮጵያን ህዝብ በቀጥታ በማሳተፍ ነው፤ ታዲያ ዶ/ር አብይ ይህን እምቅ የመፍትሄ ሃይል ለመጠቀም ምን እርምጃ ይወስዱ ይሆን? ለዚህ የሚያበቃ ቆራጥነትና እምነት ገንብተው ይሆን? እንግዲህ የጇጋማ ኬሎ የአብዲሳ የገበየሁ የባልቻ አባ  ነብሶ ልጅ መሆናቸውን ያሳዩን!!!

ዛሬ የዚህ አሳፋሪ ታሪክ መሞቻ መባቻ ላይ እየደስን የመጣን ይመስለኛል፤ ስለዚህ እነ አቦይ ስብሃት እና አባይ ጽሃዬ ያላደረጉትን ዶ/ር አብይ ያደርጉት ይሆናል የሚል ተስፋ ከፊታችን ቆሞዓል፤ ዶ/ር አብይ ከማንም በላይ ለትግራይ ህዝብ መድህን የሚሆኑበት እድል ከጃቸው ገብትዋል፤ በወያኔ ሃርነት ትግራይ መሪዎች ስግብግብነት እና አርቆ አለማሰብ ምክንያት በትግራይ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ቅሬታ ውስጥ በመግማት ላይ ያለውን ህዝብ ከትግራይ ህዝብ ጋር በማስታረቅ ወደ ነበረው ፍቅር ይመልሱታል  ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

በመጨረሻም በተቃውሞው ትግል ውስጥ በድርጅትም ሆነ በግል ለቆየነው ሃይሎች ሁለት አንጻራዊ ነገሮችን ማንሳት እፈልጋለሁ፤
ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ አንዳንድ ሃይሎች የሰሩትን ስህተት እንዳንደጋግመው፤ አደራ ዘለን እንዳንለጠፍ!  ከታሪካችን እንደምንማረው ወያኔ ኢህአዴግ አንዳንድ ነገሮችን ጣል ሲያደርግ ያችን ለመቀራመት እየዘለሉ የሚለጠፉ ጉዶች አይተናል፤ መቼም አሁንም ይህ ስህተት አይከሰትም ለማለት አልደፍርም፤ ግን ገና ጠ/ሚኒስትር ተቀየረ ብለን የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ሳይመለስ፤ በየጎሬው የታሰሩ ወገኖቻችን ሳይፈቱ፤ አስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ ምህዳር ሳይፈጠር፤ የሃገራዊ ዕርቅ መንገድ ሳይጀመር ዛሬም ወያኔ ኢህአዴግን "እንሞክረው" የሚሉ ሃይሎች ካሉ የህዝብን ትግል እና መስዋእትነት የሚያዋርድ ቅሌት ይሆናል፤ ቅሌቱ ዋጋ ስለሚያስከፍል ከዚህ አንጻር ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ትግል የደረሰበት ደረጃ እና እየተገኘ ያለው ውጤት ቀላል ባለመሆኑ ይህን ግምት ውስጥ ከማስገባት ይልቅ "እኛ በያዝነው መንገድ ብቻ ካልሆነ፤ የኛ ሃሳብ ብቻ ትክክል ነው" በሚል ግትር አካያሃድ የተገኘውን ውጤት ቢያንስ በታክቲክ ደረጃ በመጠቀም የስትራቴጅያዊ ግባችን ግብዓት እንዳናደርገው አደናቃፊዎች እንዳንሆን ረጋ ብለን እናስብ። አንዳንዴ በታሪክ ውስጥ ግለሰቦች ልዩ እድል የሚያገኙበት ወቅት አለ፤ ለዚህም እንደ ምሳሌ የማቀርበው ሚካኤል ጎርባቾብን ነው፤ ጎርባቾብ ለረዢም ዘመን በሶቢየት ህብረት ላይ ተጭኖ በሶሻሊዝም ስም የሶብየት ህብረትን ህዝብ ሲቀልድበት የነበረው "ኮሚኒስት ፓርቲ" አባል እና መሪ የነበረ ቢሆንም በሃገሪቱ የተተከለውን የሶሽልኢምፔርያሊስት አምባገነናዊ አገዛዝ ለማፈራረስ ምክንያት ሆኖአል። የተጠላው "ኮሚኒስት ፓርቲ" መሪዎች እና አገልጋዩ የስለላ መዋቅር(ኬጅቢ) የህዝብን አመጽ መቋቋም አልቻሉም።  ዶ/ር አብይም በተመሳሳይ የታሪክ ገጠመኝ ላይ የኢትዮጵያ መሪ ሆነዋል እንግዲህ የሚሄዱበት መንገድ ሊፈተሽ መድረኩን ይዘዋል። ፈጣሪ ቅን ልቦና ይስጣቸው!! እኛም ስሜታዊ ሳይሆን ምክንያታዊ እንሁን።

ከ ተስፋሁን _ አትላንታ March 2018